# <u>ሕመምሽ አመመኝ</u>

አሥራደው (ከፈረንሳይ)



አንቺን ስከረክም - አንቺኑ ስኳኩል፤
ደስታሽን ሳነሳ - ሃዘንሽን ስጥል፤
እራብሽ ሲርበኝ፤
ጥማትሽ ሲጠማኝ፤
ሲያምሽ እየታመምኩ፤
ስትድኝ እየዳንኩ፤
አንቺን እያነሳሁ፤
አንቺኑ እያሰላሁ፤
እኔን እኔን ሳልሆን - አንቺን አንቺን እያልኩ፤
ያባቴን ስም ትቼ - ባ'ቺ ስም እየማልኩ፤
ከሳሁ መነመንኩኝ - ሸክምሽ ከበደኝ፤
ጭንቅሽ አስጨንቆ - ሃዘንሽ ተጫነኝ፤
መከራሽ በርክቶ ፡ ሕመምሽ አመመኝ::

ጉስቁልናሽ በዝቶ፤
ችግርሽ በርክቶ፤
ስብዕናሽ ተረስቶ - ሃዘንሽ ቅጥ አቶ፤
ሞ - ትሽ አልል አለሽ፤
አ - ለሽ አልል የለሽ፤
አንቺን ሳንቆራጥጥ - ሳነሳ ሳስቀምጥ፤
በመከራሽ ስበግን - በችግርሽ ሳምጥ፤
ከፊትሽ ሳነበው ፡ ጭንቅሽ አስጨንቆኝ፤
መከራሽ በርክቶ ፡ ሕመምሽ አመመኝ ::

*ሆነና !*
*ማስፈራሪያ ፊትሽ - መለመኛ ስምሽ፤*
*አንገትሽ ተራቁቶ - ተቆርጦ ማተብሽ፤*
*አንድ ሁለት ተብሎ - ሲቆጠር ጎድንሽ፤*
*አንጀትሽ ተጣብቆ - ሲሟገት ከጀርባሽ፤*
*የልጅ ያለህ ብለው - ሲያለቅሱ ጡቶችሽ፤*
*ወቀሰኝ ሕሊና፤*
*ታዘበኝ ሰብዕና፤*
*አመመኝ ህመምሽ፤*
*ደቆሰኝ ሃዘንሽ፤*
*በራብሽ ተራብኩኝ - ጥማትሽ አስጠማኝ፤*
*ካንቺ በመራቄ ፡ ሕሊና ወቀሰኝ፤*
*መከራሽ በርክቶ ፡ ሕመምሽ አመመኝ፡፡*

*ሃዘንሽ አስከፋኝ፤*
*ደስታሽ እራቀኝ፤*
*ፈገግታሽ ናፈቀኝ፤*
*መከራሽን ጠላሁ፤*
*ምቾትሽን ተመኘሁ፤*
*ጥምሽን ልጠማ - እራብሽን ልራበው፤*
*ሸክምሽን ልሸከም - ጀርባሽን ይቅለለው፤*
*ካንቺ በመራቄ - ሕሊና ወቀሰኝ፤*
*አገሬ ልንገርሽ - ሕመምሽ አመመኝ፤*
*አገሬ ልንገርሽ - ሕመምሽ አመመኝ፤*
***አገሬ !***

*የአገራቸው የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጉዳይ ለሚያስጨንቃቸው አገር ወዳድ ወገኖች ሁሉ ማስታወሻ ትሆን ዘንድ የተቋጨች ::*

*ሃምሌ 8 ቀን 2005 ዓ.ም. (15/ 07/2013)*